# የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ፖሊሲ

**(ረቂቅ)**

**የካቲት 2013 ዓ.ም**

**አዲስ አበባ**

## ማውጫ

ርዕስ
ገጽ

1. መግቢያ ........ 1
2. የፖሊሲው ርዕይ፣ ተልዕኮ እና ዓላማዎች ........ 2
2.1 ርዕይ ........ 2
2.2 ተልዕኮ ........ 2
2.3 ዓላማዎች ........ 2
**3. የፖሊሲው አቅጣጫዎችና ስትራቴጂዎች** ........ 3
3.1 የሰው ሀብት ልማት ........ 3
3.2 የቴክኖሎጂ ልማት፣ ሽግግር እና የእዉቀት አስተዳደር ........ 5
3.3 ምርምርና ልማት ........ 7
3.4 ኢኖቬሽን እና የኢንተርፕራይዞች ተወዳዳሪነት ........ 8
3.5 የፋይናንስ አቅርቦት፣መዋዕለ-ንዋይ፣ ድጋፍና ማበረታቻ ........ 9
3.6 ጥራትና አዕምሯዊ ንብረት ........ 11
3.7 ትብብር እና ትስስር ........ 13
3.8 አካባቢዊ፣ ማህበራዊና ባህላዊ ልማት ........ 14
4 የፖሊሲው አተገባበርና መርሆዎች ........ 16
5 የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን አስተዳዳር ሥርዓት ........ 16
5.1 የመንግስት ሚና ........ 17
5.2 የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ምክር ቤት ሚና ........ 17
5.3 የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ዘርፍ እና ሌሎች የኢኖቬሽን ሥርዓቱ ተዋናዮች ........ 17
5.4 የግሉ ዘርፍ ሚና ........ 18
5.5 አጠቃላይ የማህበረሰቡ ሚና ........ 18
6 የክትትል፣ ግምገማና የድጋፍ ሥርዓት ........ 18
6.1 ክትትልና ግምገማ ........ 18
6.2 ለፖሊሲው አፈፃፀም የድጋፍ ሥርዓት ........ 19

## 1. መግቢያ

ሀገራት የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን በመጠቀም የኢኮኖሚና ማህበራዊ ዕድገታቸውን ፈጣን ቀጣይነት ያለው እና ተወዳዳሪ ማድረግ እንደቻሉ የዕድገት ታሪካቸው ያሳያል። በቅርብ ዓመታት ውስጥ አስደናቂና ፈጣን እድገት ያስመዘገቡት የደቡብ ምሥራቅ እስያ ሀገራት ስኬት ዋናው ምክንያት ሀገራቱ የቴክኖሎጂ እውቀትና ክህሎትን በመጠቀም ገበያ መር ኢኮኖሚን መገንባታቸውና የቴክኖሎጂ አቅም ማካበታቸው መሆኑ አንዱ ማሳያ ነው። በሌላ በኩል የ2030 የዘላቂ ልማት ግቦችን እንዲሁም የአፍሪካ 2063 አጀንዳን ለማሳካት የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ወሳኝ ድርሻ እንዳለው ተመላክቷል።

ሀገራችን ሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ እና ኢኖቬሽን መዋቅራዊ የኢኮኖሚ ሽግግር ለማምጣትም ሆነ እድገቱን ቀጣይ ለማድረግ የሚኖረውን ሚና በመገንዘብ በ2004 ዓ.ም. ትኩረቱን በመካከለኛ ትላልቅ የማምረቻና አገልግሎት መስጫ ተቋማት ውስጥ ቴክኖሎጂን መጠቀም፣ መቅዳትና ማላመድ ያደረገ ፖሊሲ በማውጣት የተለያዩ ጥረቶች ሲደረጉ ቆይተዋል። በፖሊሲው አፈጻጸም ሂደት የተገኙ ውጤቶች ቢኖሩም መሰረታዊ ለውጥ በማምጣት ረገድ ግን ስኬታማ እንዳልነበር መረዳት ተችሏል። ከ2012 ዓ.ም አንስቶ ተግባራዊ የሆነው ሀገር በቀል የኢኮኖሚክ ማሻሻያ አጀንዳ ቀድሞ የልማት እድሎች ተደርገው ይወሰዱ ከነበሩት ከግብርና እና ከማኑፋክቸሪንግ በተጨማሪም ቱሪዝም፣ ማዕድን እና አይሲቲ አስቻይ የሆነባቸው አገልግሎቶችን አዳዲስ የልማት ምንጮች አድርጎ ወስዷል። የኢኮኖሚ ማሻሻያ ዋና ዋና ግቦች የስራ እድል መፍጠር፣ የሀገሪቱን የውጭ ገቢ መጨመር፣ የአጠቃላይ ሀገራዊ ምርትን ማሳደግ፣ አዳዲስ ሀብት መፍጠር እና ወደ አካታች ብልጽግና መገስገስ ነው። ለዚህ ርዕይ ስኬት ደግሞ ኢኖቬሽን እንደ ወሳኝ የማስፈጸሚያ መሳሪያ ጥቅም ላይ እንደሚውል ተገልጿል።

በዚሁ መነሻነት ለአዳዲስ ለውጦች እና ፍላጎቶች ምላሽ መስጠት የሚችል እና የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ልማትን የሚያፋጥን ፖሊሲ ማዘጋጀት አስፈላጊ እንደሆነ ታምኖበታል። በፖሊሲው ዝግጅት ሂደት የዘርፉ ነባራዊ ሁኔታዎች፣ የሀገራት ተሞክሮ፣ የ10 ዓመቱ ሀገራዊ የልማት እቅድ እና ሌሎች ተዛማጅ ሰነዶች በግብዓትነት ተወስደዋል። ፖሊሲው የታለመለትን ዓላማ ማሳካት እንዲችል የሰው ኃብት ልማት፤ ትብበርና ትስስር፤ የፋይናንስ አቅርቦትና ማበረታቻ፤ ምርምርና ልማት፤ ጥራትና አእምሯዊ ንብረት፤ አካባቢያዊ ማህበራዊና ባህላዊ ልማት፤ የቴክኖሎጂ ልማትና ሽግግር፤ ኢኖቬሽንና የኢንተርፕራይዞች ተወዳዳሪነት ወሳኝ

የፖሊሲ ጉዳዮች ተደርገው ታይተዋል፡፡ ለተለዩት ወሳኝ ጉዳዮች ግቦች እና የማስፈጸሚያ ስልቶች ተዘጋጅተውላቸዋል፡፡

## 2. የፖሊሲው ርዕይ፣ ተልዕኮ እና ዓላማዎች

### 2.1 ርዕይ

የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ፖሊሲ ርዕይ የተቀረፀው "ሀገራችን ለአፍሪካ የብልፅግና ተምሳሌት ሀገር ሆነ ማየት ነው" ከሚለው መነሻ ሲሆን የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ፖሊሲ ርዕይ የሚከተለው ነው፡፡

**"በሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ልማት ተምሳሌታዊ ሀገር"**

### 2.2 ተልዕኮ

ለሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ምቹ ሥነ-ምህዳር በመፍጠር፤ ዘርፉ ለሥራ ዕድል እና ለሀብት ፈጠራ እንዲሁም ለአጠቃላይ ሀገራዊ ምርት ዕድገት ያለውን ድርሻ በማሳደግ የህብረተሰቡን ኑሮ በዘላቂነት ማሻሻል፡፡

### 2.3 ዓላማዎች

የፖሊሲው ዋና ዋና ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. ፍላጎትን መሰረት ያደረገ እና የቀጣይ ዘመን ኢንዱስትሪ ውስጥ በብቃት የሚሳተፍ የሰው ኃይል የሚፈጠርበትን ሥርዓት መዘርጋት፤
2. ለሳይንስና ቴክኖሎጂ ምርምር፣ እንዲሁም ለኢኖቬሽን መደላድል ለመፍጠር የሚያስችል መሰረተ-ልማቶችን በቀጣይነት ማልማት፤
3. ሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ቢዝነስን መሠረት ያደረጉ ኢኖቬሽኖችን በማበረታታት ለስራ ዕድል፣ ለሃበት ፈጠራና ለአጠቃላይ ሀገራዊ ምርት (GDP) ዕድገት የሚኖረውን ድርሻ ማሳደግ፤
4. በቴክኖሎጂ ልማትና ኢኖቬሽን የግሉን ዘርፍ ሚና በማሳደግ መሪነቱን ማረጋገጥ፤
5. የሀገር በቀል ዕውቀቶችን በማልማት ጥቅም ላይ ማዋል የሚያስችል የአደረጃጀት እና የአሠራር ሥርዓትን በመፍጠር የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ባህል መገንባት፤
6. የተቋማት ትስስርና ትብብርን በማጠናከር ሀገራዊ፣ አህጉራዊና ዓለምአቀፋዊ አጋርነት እና ተጠቃሚነትን ማሳደግ፤

7. ምቹ የሳይንስ፣ የቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ሥነ-ምህዳር እንዲፈጠር የሚያስችሉ የሕግና የአሠራር ማዕቀፎችን መዘርጋት፤

## 3. የፖሊሲው አቅጣጫዎችና ስትራቴጂዎች

በፖሊሲው ዝግጅት ሂደት የዘርፉ ነባራዊ ሁኔታዎች፣ የሀገራት ተሞክሮ፣ የ10 ዓመቱ ሀገራዊ የልማት እቅድ እና ሌሎች ተዛማጅ ሰነዶች በግብዓትነት ተወስደዋል፡፡ ፖሊሲው የታለመለትን ዓላማ ማሳካት እንዲችል የሰው ኃብት ልማት፤ ትብበርና ትስስር፤ የፋይናንስ አቅርቦትና ማበረታቻ፤ ምርምርና ልማት፤ ጥራትና አእምሯዊ ንብረት፤ አካባቢያዊ ማህበራዊና ባህላዊ ልማት፤ የቴክኖሎጂ ልማትና ሽግግር፤ ኢኖቬሽንና የኢንተርፕራይዞች ተወዳዳሪነት ወሳኝ የፖሊሲ ጉዳዮች ተደርገው ታይተዋል፡፡ ለተለዩት ወሳኝ ጉዳዮች ግቦች እና የማስፈጸሚያ ስልቶች ተዘጋጅተውላቸዋል፡፡

### 3.1 የሰው ሀብት ልማት

### አጠቃላይ ምልከታ

በሀገራችን ነባራዊ ሁኔታ በሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን፣ የምርምርና ልማት በሀገር ውስጥም ይሁን በውጭ የሚገኙ ቴክኖሎጂዎችን ለመጠቀም የሚያስችል የዕውቀትና የክህሎት አቅም እንዲሁም የአመለካከት ውስንነት በስፋት ይስተዋላል፡፡ ከሌሎች ሀገሮች ተሞክሮ እንደምንረዳው ለሀገር ኢኮኖሚ ዕድገት መሰረታዊ ጉዳይ ሳይንስ፤ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን መጠቀም እና መፍጠር የሚያስችል የሰው ሀይል ማልማት ነው፡፡ ስለሆነም ከመሰረታዊ እስከ ከፍተኛ ትምህርት ድረስ በሳይንስ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን የተቃኘ መሰረታዊ የሰው ሃብት ልማት አንዲገነባ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ ከዚህ በተጓዳኝ መጻኢውን ጊዜ ማዕከል ያደረገ የሰው ሀይል እዲገነባ ጎን ለጎን ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት ይተገበራል፡፡ በተጨማሪም ከሰው ሃይል ልማት አኳያ የሳይንስ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን እንቅስቃሴን በብቃት መምራት የሚችል የሰው ሃይል ይገነባል፡፡ እንዲሁም ለዜጎች የተለያዩ የሳይንስ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ባህል ግንባታ ሊፈጥሩ የሚችሉ ከመደበኛው የትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራሞች በተጓዳኝ የማህበረሰብ ልማት ተግባራት ይከናወናሉ፡፡ በመሆኑም ከሰው ኃይል ልማት አኳያ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ግቦች እና ስትራቴጂዎች ተለይተዋል፡፡

## ግብ 1፡- በሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን የመጠቀም ባህሉ የጎለበተ ዜጋ ማፍራት

**የአፈፃፀም ስልት፡-**

- ህብረተሰቡ በሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ያለውን ግንዛቤ ለማሳደግ የሚያስችሉ የአህዝቦት ሥራዎች ይተገበራሉ፤
- በአጠቃለይ የትምህርት ሥርዓት ውስጥ ተግባር ተኮር የሳይንስና ቴክኖሎጂ ትምህርት ሥነ-ምህዳር ይፈጠራል፤

## ግብ 2፡- ለሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን አመራር የሰው ሃይል ማልማት

**የአፈፃፀም ስልት፡-**

- የሥራ ፈጠራና እርካታ እንዲኖር ምቹ ሁኔታን መፍጠር የሚችል የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን አመራር ብቃት የማሳደግ ሥራዎች ይሰራሉ፤
- መልካም አጋጣሚዎችን በመጠቀም ምቹ ስነ-ምህዳር መፍጠር የሚችል የምርምርና ልማት የአመራር ብቃት የማሳደግ ሥራዎች ይሰራሉ፤

## ግብ 3፡- ተነፃፃሪ ጥቅም በምናገኝባቸው ዘርፎች መጻኢውን ጊዜ መሠረት ያደረገ የሰው ሃብት ማልማት

**የአፈፃፀም ስልት፡-**

- ለሀገራችን ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታ ያላቸው የመጻኢ ጊዜ የሰው ኃይል ፍላጎት በመለየት ልዩ ትምህርትና ሥልጠና እንዲሰጥ ይደረጋል፤
- ልዩ ተሰጥኦና ተውህቦ ላላቸው ዜጎች የሰው ኃብት ልማት ስርዓት ይዘረጋል፤
- የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ሥርዓተ-ትምህርት የገበያውን ፍላጎት እና አዳዲስ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዕድገቶችን ያገናዘበ እንዲሆን ይደረጋል፤

## ግብ 4፡- በሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን የሙያ ዘርፎች ብቁና በቂ ባለሙያዎች ማፍራት

**የአፈፃፀም ስልት፡-**

- የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎችና መምህራን በልማት ተቋማት የተግባር ልምምድ እንዲያደርጉ፤ እንዲሁም በልማት ተቋማት የሚሰሩ ባለሙያዎች ለከፍተኛ ተቋማት የሚያስተምሩበትንና ልምዳቸውን ለተማሪዎች የሚያካፍሉበት ስልት ይፈጠራል፤

- በሳይንስና ቴክኖሎጂ የላቀ ዕውቀትና ክህሎት ያላቸውን ቴክኒሺያኖች፣ መሀንዲሶችን የሚያፈልቁ ተቋማትን የጥራት ደረጃ እንዲያድግ፤ ቁጥራቸውን እንዲበራከት እና አክሬዲትድ (Accredited) እንዲሆኑ ይደረጋል፤
- ዜጎች ቀጣይነት ያለው የህይወት ዘመን ትምህርት (lifelong learning) እንዲያገኙ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፤
- በሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ዘርፍ የተመራማሪ ቁጥር ማሳደግ የሚያስችሉ ሀገራዊ ፕሮግራሞች ተግባራዊ ይደረጋሉ፤

## 3.2 የቴክኖሎጂ ልማት፣ ሽግግር እና የእዉቀት አስተዳደር

ቴክኖሎጂ ለአንድ ሀገር ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ዕድገት ዓይነተኛ ሚና ሊጫወት የሚችለው ወደ ህበረተሰቡ ሲሰርጹ እና በኢኖቬሽን ሲታገዙ ነው፡፡ ለኢኖቬሽን የሚያስፈለገው ዕውቀት ምርምሮችን በማካሄድ በሀገር ውስጥ ሊመነጭ ወይም በሌሎች በቀደሙ ሀገሮች የመነጨ ዕውቀቶችን በማሸጋገር እና በማዳበር ይገኛል፡፡ ሆኖም በሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ወጥ የሆነ የቴክኖሎጂ ሽግግር ስርዓት የለም፡፡ በግዢም ሆነ በምርምር የሚገኙ የቴክኖሎጂ ዕውቀቶችን ለማሰባሰብ ፣ ለማከማቸት እና ለማሰራጨት የሚያስችል ስርዓት አለመኖሩ ሀገሪቱ ቴክኖሎጂና ዕውቀትን ለማከማቸትም ሆነ ከተከማቹ ዕውቀቶች የሚገባውን ጥቅም ማግኘት አልቻለችም፡፡ በተጨማሪም የቴክኖሎጂ ሽግግር ስልቶችን ከመለየት ጀመሮ እስከ አጠቃቀም ድረስ ክፍተቶች ይታያሉ፡፡ በስራ ላይ የዋሉ ቴክኖሎጂዎችን ከተግባር ዕውቀት በመነሳት በየግዜው ለማሻሻል የሚደረግ ሙከራም ሆነ የአሰራር ስርዓት የለም፡፡ ይህም መሆኑ ቴክኖሎጂ ስራ ላይ ከዋለ በሁዋላ ፈጠራን በማከል ቀጣይ ተክኖሎጂዎችን በመፍጠር የተሸለ እሴት ለመፍጠር የሚያስችል ሁኔታ የለም፡፡የቴክኖሎጂ መሳሪያዎች የአገልግሎት ግዜያቸው ሲያልቅም የሚወገዱበት ስረአት ሊበጅ ይገባል፡፡ የማሰወገዱ ሂደት ቴክኖሎጂው ወደስራ ከሚገባበት ግዜ ጀምሮ ሊታሰብበት እና በስረአት መፈጠም አለበት፡፡ በአገራችን ሁኔታ በአግባቡ የተዘረጋ መሰል ስረአት ስለሌሌ ከቴክኖሎጂዎች የሚመጡ ጉዳቶችን ለማስቀም አልተቻለም፡፡

በተጨማሪም ቴክኖሎጂ በሀገር ኢኮኖሚ ጉዳይ ላይም ሆነ የሀገርን ደህንት በማስከበርም ረገድ ትልቁን ሚና እንዲጫወት መንግስት በሚከተሉት ግቦች እና ስትራቴጂዎች ላይ ይሰራል፡፡

## ግብ 1፦ ቴክኖሎጂ የመለየት፣ የማስገባት፣ የመማር፣ የመጠቀምና የማስወገድ አቅም ማሳደግ

**የአፈፃፀም ስልቶች**

- የቴክኖሎጂ ልየታ፣ ማስገባት፣ አጠቃቀምና አወጋገድ ስርአት ይዘረጋል፤
- ቴክኖሎጂዎች ተገቢዉ የኮዲፊከሽን ስራዎችና የዋጋ ትመና እንዲሰራላቸው ይደረጋል፤
- ሀገሪቱ ወደፊት በአለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪና ቀዳሚ የሚያደርጓትን የቴክኖለጂ አቅም/strategic technolgies/ ከወዲሁ የመለየትና ተግባራዊ የማድረግ ሥራ ይሰራል፤

## ግብ 2፡ በየዘርፉ የቴክኖሎጂ ልማትን ሽግግር ክላስተሮች እንዲፈጠሩ ማድረግ

**የአፈጻጸም ስልት**

- በቅድሚያ ሊታዩና ሰፊ የሥራ ዕድል ሊፈጥሩ የሚችሉ ቴክኖሎጂዎች ክላስተር ይዘጋጃል፤
- የገበያ ትስስር እና የዕሴት ሰንሰለትን መሰረት ያደረጉ የቴክኖሎጂ ልማትና ሽግግር ክላስተር እንዲፈጠር ይደረጋል፤
- የኢንዱስቱሪ ፓርኮች የቴክኖሎጂ ሽግግር ክላስተር እንዲፈጠር ይደረጋል፤

## ግብ 3፡- ብሄራዊ የቴክኖሎጂ መረጃ አያያዝ ሰርአት መገንባት

**የአፈጻጸም ስልት**

- ብሄራዊ የቴክኖሎጂ መረጃ ማዕከል እንዲጠናከር ይደረጋል፤
- የመረጃ አሰባሰብ፣ ሥርጭት እና አጠቃቀም የሕግ ማዕቀፍ ይዘጋጃል፤
- የቴክኖሎጂ እዉቀት አስተዳደር ስርአት ይዘረጋል፤

## ግብ 4:- የቴክኖሎጂ አቅም ከምችትንና የዕዉቀት ሽግግሩን ማሳለጥ

**የአፈፃፀም ስልቶች**

- የቴክኖሎጂ ልማት ላይ ትኩረት የሚያደርጉ የምርምር ዩኒቶች (Technological research units) በማምረቻና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት እንዲቋቋሙ ድጋፍ ይደረጋል፤

- ምርታማና ተወዳደሪ የሚያደርጉን ቴክኖዎጂዎች ላይ ትኩረት ተሰጥቶ ይሰራል፤
- የሀገር በቀል ቴኖሎጂዎችን ለመጠቀምና ለማሳደግ የሚያስችል ስርዓት  ይዘረጋል፤

## 3.3 ምርምርና ልማት

**አጠቃላይ ምልከታ**

የሀገራችን የምርምር ሥነ ምህዳር የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ልማት ለማፋጠን የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት እንዲኖር ከማድርግ፤ እንዲሁም የምርምር መስረት ልማትን ከማሟላት አንጻር በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል። በመሆኑም  በኢትዮጵያ ሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ለልማት የመጠቀም እንቅስቃሴ ውጤታማ እንዲሆን የተጠናከረ የምርምርና ልማት ስርዓት ሊኖር ይገባል። በሀገራችን ውስጥ የሚከናወኑ ምርምሮች በዋናነት የሀገሪቱን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች የሚፈቱና ለልማት ግቦች መሳካት አስተዋፅኦ የሚያደርጉ እንዲሆኑ ይፈለጋል። በተጨማሪም የምርምር ተቋማት በሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ላይ ትኩረት አድርገው እንዲሰሩ በሚያስችል መልክ አቅማቸውን መገንባት አስፈላጊ ነው። ከዚህ ጋር ተያይዞ ለሳይንስና ቴክኖሎጂ ምርምር፣ እንዲሁም ለኢኖቬሽን መደላድል ለመፍጠር የሚያስችል መሰረተ-ልማቶችን በቀጣይነት ማልማት ይጠበቃል። በሌላ በኩል በኢንዱስትሪዎች፣ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና በምርምር ተቋማት መካከል የጋራ ምርምሮች እንዲከናወኑ ይደረጋል። በመሆኑም የዚህ ቁልፍ ፖሊሲ ጉዳይ ዋነኛ ተልዕኮ እነዚህን ችግሮች በመቅረፍ የምርምር ሥራዎችን ውጤታማ ለማድረግ የሚሰራ ይሆናል።

**ግብ 1፡- ከሀገራችን የዕድገት ፍላጎት ጋር የተጣጣሙ ችግር ፈቺ የምርምር ውጤቶችን ማሳደግ**

**የአፈፃፀም ስልት፡**

- የሀገሪቱን የልማት ፍላጎት የሚያሟሉ የሳይንስ፣ የቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ምርምሮች እንዲከናወኑ ይደረጋል፤
- በሀገሪቱ የሚከናወኑ ምርምሮችን የሚያቅድ፣ የሚገመግምና የሚደግፍ ተቋም ይደራጃል፤
- የምርምር ግራንት አሰጣጥ፣ የተመራማሪዎች ማበረታቻ፣ የጉምሩክና የግዥ ሥርዓትን ያካተተ ምቹ የምርምር ሥነ-ምህዳር ይፈጠራል፤

**ግብ 2፡- የምርምር መሠረተ ልማት አቅሞችን ማሳደግ**

**የአፈፃፀም ስልት፡-**

- ሀብትን በጋራ ለመጠቀምና የዘመነ ምርምር ለማካሄድ የሚያስችሉ ማዕከላዊ ላብራቶሪዎች እንዲቋቋሙ ይደረጋል፤
- የምርምር መሰረተ ልማቶች እንዲሟሉና እንዲጠናከሩ ይደረጋል፤
- ለምርምርና ስርፀት በቂ በጀት እንዲመደብ ይደረጋል፤

**ግብ 3፡- የግሉን ዘርፍ በምርምርና ልማት የሚኖረውን ሚና ማሳደግ**

**የአፈፃፀም ስልት፡**

- የግሉ ዘርፍ በምርምር ተግባራት የሚሳተፍበት የድጋፍና የማበረታቻ ማዕቀፍ ይዘጋጃል፤
- የግል የምርምር ተቋማት እንዲያቋቁሙና እንዲበራከቱ ይደገፋሉ፤

## 3.4 ኢኖቬሽን እና የኢንተርፕራይዞች ተወዳዳሪነት

የአንድ ሃገር አለምአቀፍ ተወዳዳሪነት ሊያድግ የሚችለዉ ምርታማ የሆነ ኢኮኖሚ መገንባትና በርካታ ተወዳዳሪ ኢንተርፕራይዞችን መፍጠር ሲቻል ነዉ፡፡ ይሁን እንጂ ኢንተርፕራይዞችን ለመፍጠርም ሆነ፣ በተለዋዋጭ የቢዝነስ ከባቢ ውስጥ ተላምደው መጓዝ እንዲችሉ የሚያግዝ የኢኖቬሽን ስነምህዳር አልተገነባም፡፡ በውጤቱም በሃገርም ሆነ በአለማቀፍ ደረጃ ብቁ እና ተወዳዳሪ ሊሆኑ የቻሉ ኢንተርፕራይዞች በብቂ መጠን መፍጠር አልተቻለም፡፡ በመሆኑም መንግስት የኢኖቬሽን ሥነ-ምህዳር በመፍጠርና የሃገሪቱን የኢኖቬሽን አቅም በማዳበር ኢኖቬሽንን በሰፊው ማልማትና በርካታ በሃገርም ሆነ በአለምአቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ ኢንተርፕራይዞችን ለመፍጠር ይሰራል፡፡ ይህም ሰፊ የሥራ ዕድሎችንና ሀብቶችን ሊፈጥር በሚችል መልኩ የሚከናወን ሲሆን፣ ለትግበራውም መንግስት በሚከተሉት ግቦች እና ስትራቴጂዎች ላይ ያተኩራል፡፡

## ግብ 1፦ የኢኖቬሽን ሥነ-ምህዳር መገንባት

**የአፈፃጸም ስልት**

- ጀማሪ ተቋማት የፍይናንስ፣ የቴክኒክ፣ የመስሪያ ቦታ እና መሰል ድጋፎች የሚያገኙበት የአሰራር ሥርዓት ይዘረጋል፤
- ለጀማሪ ተቋማት (Technology startups) የገበያ ዋጋ ትመና እና የኢንቨስትመንት የአሰራር ስርአት ይዘረጋል፤
- ስትራቴጂካዊ ተፈላጊነት ባላቸው የቴክኖሎጂ መስኮች የግልና የመንግስት አጋርነት ሥርዓት ይዘረጋል፤
- በጥናት ላይ የተመሠረተ የእሴት ሰንሰለት እና የኢኖቬሽን ክላስተሪንግ አሰራር እንዲስፋፋ ይደረጋል፤
- ውጤታማነታቸው የተረጋገጠና ወደ ምርትና አገልግሎት የተቀየሩ የቴክኖሎጂ ውጤቶች በመንግስት የግዥ ሥርዓት ውስጥ እንዲታቀፉ ይደረጋል፤

## ግብ 2፦ ቴክኖሎጂን መሠረት ያደረጉ በሃገርና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሆኑ ኢንተርፕራይዞችን መፍጠር

**የአፈጻጸም ስልት**

- ኢንተርፕራይዞች ቴክኖሎጂን መሰረት አድርገው ምርታማነትን እንዲያሳድጉ የሚደግፉ ልዩ ተቋማት ይመሰረታሉ፤
- ወደ ዉጪ ለሚልኩ፣ የገቢ ምርትን ለሚተኩ እንዲሁም ወደ ሌሎች ሃገራት ለሚስፋፉ የቴክኖሎጂ ኢንተርፕራይዞች የማበረታቻ፤ የድጋፍና የክትትል አሠራሮች ይዘረጋሉ፤

## 3.5 የፋይናንስ አቅርቦት፣መዋዕለ-ንዋይ፣ ድጋፍና ማበረታቻ

**አጠቃላይ ምልከታ**

የሳይንስ ቴክኖሎጂ እና ኢኖቬሽን ተግባራት ሀሳብን ከማፍለቅ ጀምረው፣ በምርምር ውስጥ አልፈው ወደ ተግባር እስኪገቡም ሆነ ወደ ተግባር ከገቡም በኋላ በገበያ ውስጥ ለመቆየት እና ውጤታማ ለመሆን የፋይናንስ አቅርቦት እና ድጋፍ ይፈልጋሉ። የፋይናንስ አቅርቦት እና ድጋፍ በማይኖሩበት ሁኔታ ሃሳቦችን ወደ ገባያ ማምጣት አዳጋች ነው። በተለምዶአዊ አሰራር በብድር እና እርዳታ ከሚገኙ የፋይናነስ ድጋፎች በተጨማሪ ዘርፈ ብዙ የሆኑ የፋይናንስ ድጋፎችን እና አቅርቦቶችን ማድረግ ያስፈልጋል። የኢኖቬሽን ስራ እየወደቀ እና እየተነሳ

በሙከራ ላይ ተመስርቶ ለገበያ የሚቀርብ ነው፡፡ ወሳኝ የሆኑ የተሳኩ የኢኖቬሽን ስራዎች ወደገበያ ከመድረሳቸው በፊት በርካታ ያልተሳኩ ሙከራዎች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ ስለሆነም ለዘርፉ የሚደረጉ ድጋፎች ይህንኑ ልዩ ሁኔታ ከግምት ያስገቡ መሆን ይጠበቅባቸዋል፡፡

ኢኖቬሽንን ከጥንስሱ ጀምሮ ወደ ገበያ ለማውጣት የሚደረጉ አማራጭ የፋይናንስ አቅርቦቶች፣ ድጋፎች እና ማበረታቻዎች በኢትዮጵያ ውስጥ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኛሉ፡፡ ኢኖቬሽን ልማትን ለመከወን ከባንክ ወይም ከግለሰብ ከሚገኝ ብድር በዘለለ አማራጭ የገንዘብ ምንጮች የሉም፤ ለምርምር ስራዎችም ቢሆን መንግስት በዩኒቨርሲቲዎች እና በምርምር ተቋማት በኩል ከሚያደረጋቸው መለስተኛ ድጋፎች ውጭ ትርጉም ያለው የፋይናንስ ድጋፍ ማግኘት ያስቸግራል፡፡ በትንሹም ቢሆን የሚገኙ የገንዘብ ድጋፎችን ጥቅም ላይ ለማዋልም ያለው የህግ ማዕቀፍ አመቺ አይደለም፡፡ በአጠቃላይ በአገሪቱ ያለው የዘርፉ ከባቢያዊ ሁኔታ በድፍረት የሚሞክሩ እና ሃሳብ እና እውቀትን ብቻ ይዘው ወደገበያ የሚወጡ የተሻለ እሳቤ ያላቸውን ስራ ፈጣሪዎችን የሚያበረታታ አይደለም፡፡ ይህም አገሪቱ ከዘርፉ ማግኘት የሚገባትን ጥቅም እንዳታገኝ አድርጓታል፡፡ ይህንን ሁኔታ ከመሰረቱ ለመቀየር መንግስት የሚከተሉትን ግቦች እና ስትራቴጂዎች መሰረት በማድረግ ይሰራል፡፡

## ግብ 1፡- ለሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ልማት የፋይናንስ አቅርቦት አማራጮችን ማስፋት

**የአፈፃፀም ስልት**

- ለሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ልማት ተደራሽ፣ አካታችና ቀልጣፋ የፋይናንስ አቅርቦት አማራጮች ይዘረጋሉ፤
- ለሳይንሳዊ ምርምር፣ ለቴክኖሎጂ ልማትና፣ ለኢኖቬሽን እንዲሁም ለቴክኖሎጂ ግብይት የሚውሉ ሀገራዊ ፋውንዴሽኖችና ፈንዶች ይቋቋማሉ፤

## ግብ 2፡- ሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽንን ለማልማት ልዩ ልዩ ማበረታዎችን ማስፋት

**የአፈፃፀም ስልት**

- ኢኖቬተሮችንና ኢንተርፕረነሮችን ለማበረታታት የሚያስችል የሪስክ ካፒታል ስርአት ይዘረጋል፤
- ለኢኖቬሽን ልማት ሥራዎች የግሉ ዘርፉ ከመንግስት በቀጥታ የገንዘብ ድጋፍ የሚየገኝበት አሰራር ይዘረጋል፤

- የተመራማሪዎች ማበራታቻ ስርዓት ይዘረጋል፤

**ግብ 3፡- የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ዘርፍን ለማልማት የንግድና የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎችን ማስፋት**

- በሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ዘርፍ ለተሰማሩ ኢንቨስተሮች ልዩ ልዩ የታሪፍ፣ የታክስ እና ተዛማጅ የፋይናንስና የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎች እንዲሰጡ ይደረጋል፤
- ለዘርፉ ዕድገት የላቀ አስተዋጽኦ የሚያበረክቱ የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ተዋናዮች እንዲበረታቱ ይደረጋል፤

## 3.6 ጥራትና አዕምሯዊ ንብረት

**አጠቃላይ ምልከታ**

በሀገራችን በደረጃ ዝግጅት፣ በተስማሚነት ምዘና፣ በሥነ-ልክ፣ በአክሬዲቴሽን እና በቁጥጥር ስራዎች የተሰማሩ የጥራት መሰረተ ልማት ተቋማት ቢኖሩም፤ እያደገ ካለው የጥራት ፍላጎት ጋር ሲነጻጸር አሁን ያሉበት አቅም ሰፊ ክፍተት የሚስተዋልበት ነው፡፡ በምርምር የታገዙ የደረጃ ዝግጅቶች እምብዛም የሚስተዋሉ ካለመሆኑም በላይ ከሳይንሳዊ ሥነ-ልክ ጋር በተያያዘ የሚደረጉ ጥረቶችም በንጽጽር ዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኙ ናቸው፡፡ በዋናነት የመንግስት ተግባር የሆነው የህጋዊ ስነ-ልክ እና የአስገዳጅ ደረጃዎችን አተገባበር የመቆጣጠር ስራ በሚጠበቀው ደረጃ የተጠናከረ ባለመሆኑ ጥራታቸውን ያልጠበቁ ምርትና አገልግሎቶች በስፋት በገበያው እንዲታዩ አድርጎ ቆይቷል፡፡ የኢንዱስትሪ ስነ-ልክ ስራዎች  የግል ዘርፉ እንዲሰማራባቸው በማድረግ፤ የደረጃ ዝግጅት፣ የስልጠና እና ቴክኒክ ድጋፍ ስራዎች በልማት ድርጅቶች እንዲከናወኑ በማድረግ፤ የተለያዩ አካላት የድርሻቸውን እንዲወጡ ማድረግ ይገባል፡፡

በተመሳሳይ የዉጭ ኢንቨስትመንት ለመሳብ በምናደርገው ጥረት ውስጥ የኢንቬስተሮችን የውሳኔ እይታ ከሚወስኑት ጉዳዮች ዋነኛው በሀገሪቱ ምን ያክል ጠንካራ የአእምሯዊ ንብረት ጥበቃ እና ህግ የማስፈጸም ስርዓት አለ የሚለው ነው፡፡ የአእምሯዊ ንብረት ባለቤትነት የሚረጋገጥበት ስርዓት በሀገራችን ቢኖርም ሀብቱ እንደ ተንቀሳቃሽ ሀብት የዋጋ ግምት ወጥቶለት ብድር ለማግኘት እንደ ማስያዣ ሲያገለግልም ሆነ በአጠቃላይ የፋይናንስ ልውውጥ አካል ተደርጎ ሲወሰድ አይታይም፡፡ በከፍተኛ ትምህርት እና በምርምር ተቋማት ውስጥ የምርምር እና ፈጠራ ስራን የሚያከናውኑ ተመራማሪዎች እና ኢኖቬተሮች ከድካማቸው

ውጤት ተጠቃሚ የሚሆኑበት ግልጽ የፖሊሲ አቅጣጫ የለም፡፡ በተጨማሪም ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፉ የመጡ የማህበረሰብ እውቀቶች ስርዓት ባለው መልኩ የሚጠኑበት፣ ጥበቃ የሚያገኙበት፣ ጥቅም ላይ የሚውሉበት እና የእውቀቱ ባለቤቶች የጥቅሙ ተጋሪ የሚሆኑበት ግልጽ ስርዓት አልተበጀም፡፡ በአጠቃላይ ከጥራት እና ከአእምሯዊ ንብረት ስርዓት ጋር በተገናኘ ያሉብንን እጥረቶች ስር ነቀል በሆነ ሁኔታ በመፍታት ሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ እና ኢኖቬሽን ለልማት ፕሮግራሞች ማስፈጸሚያ እንዲሆን ለማድረግ.መንግስት የሚከተሉትን የአፈጻጸም ስልቶች ነድፎ የተቀመጡትን ግቦች ለማሳካት ይሰራል፡፡

**ግብ 1፡-** የጥራት መሰረተ ልማት ተቋማት ዓለምአቀፍ ደረጃቸውን ማሳደግ

- አገልግሎትን ለተጠቃሚ ማቅረብ ላይ ያተኮሩ የጥራት መሰረተ ልማት ስራዎች በግሉ ዘርፍ እና በልማት ድርጅቶች እንዲሰሩ ይደረጋል፤
- በሀገር ውስጥ የምርምር ውጤት ላይ ላተኮሩ የደረጃዎች ዝግጅት እና የሳይንሳዊ ስነ-ልክ ወሰንን በጥልቀት እና በስፋት ለሚደረጉ ምርምሮችና ተዛማጅ ሥራዎች ድጋፍ ይደረጋል፤
- ሀገራዊ የጥራት መሠረተ-ልማትን ሥራ ላይ ለማዋል የሚያስችል ጠንካራ የአክሪዲቴሽን፣ የቁጥጥር እና የማስፈፀም አቅም ይገነባል፤

**ግብ-2፡-** በጥራትና ደረጃዎች አተገባበር የግሉን ዘርፍ ተሳትፎ ማጎልበት

- በተጠቃሚው ተፈላጊ የሆኑ የጥራት ደረጃዎችን በማሟላት በአለም ገበያ ምርትና አገልግሎታቸውን የሚያቀርቡ ኢንተርፕራይዞች የሚበረታቱበት ስርዓት ይዘረጋል፤
- የግል ዘርፉ በኢንዱስትሪያዊ ስነ-ልክ፣ በተስማሚነት ምዘና፣ በስልጠና እና በቴክኒክ እገዛ ስራዎች እንዲሰማሩ ድጋፍ ይደረጋል፤

**ግብ 3፡-** ሀገር በቀል የማህበረሰብ ዕውቀቶችን ማልማትና ተጠቃሚነትን ማሳደግ

- የሀገር በቀል የማህበረሰብ ዕውቀቶች እና በኢንዱስትሪያዊ አመላካች የሚገለጹ ሀብቶቻችን በጥናት የሚለዩበት፤ በአእምሯዊ ንብረት ጥበቃ ስርዓት ውስጥ የሚካተቱበት፤ ጥቅም ላይ የሚውሉበት እና የእውቀቱና የሀብቱ ባለቤቶች የጥቅሙ ተጋሪ የሚሆኑበት አካታች ስርዓት ይዘረጋል፤
- የጄኔቲክ ሀብቶቻችንና የማህበረሰብ ዕዉቀቶች በሌሎች አካላት ጥቅም ላይ ከመዋላቸው በፊት የሃገራችንን ቅድመ ስምምነት እንዲያገኙና ከሚገኘው ጥቅምም ተጋሪነታችንን በሚረጋገጥበት ሁኔታ ይተገበራሉ፤

**ግብ 4፡- የአእምሯዊ ንብረት ጥበቃ ሥርዓቱ ምርምር እና ኢኖቬሽንን በሚደግፍበት አግባብ ማጠናከር፤**

- የአእምሯዊ ንብረት ባለቤትነት ማረጋገጫ ላገኙ ቴክኖሎጂዎች የዋጋ ትመና ስርዓት ይዘረጋል፤ ብድር ለማግኘት እንደ ማስያዣ በመጠቀም ለፋይናንስ ልውውጥ እንዲውል ይደረጋል፤
- በኢንዱስትሪዎች፣ በከፍተኛ ትምህርት እና በምርምር ተቋማት ተማራማሪዎችና ኢኖቬተሮች ተጠቃሚ የሚሆኑበት ተቋማዊ የአምሯዊ ንብረት ፖሊሲ ይቀረፃል፤
- ለውጭ ገበያ ለሚቀርቡ ምርትና አገልግሎቶች በመዳረሻ ሀገራት በጥናት ላይ የተመሰረተ የአእምሯዊ ንብረት ጥበቃ እንዲያገኙ ድጋፍ ይደረግላቸዋል፤

## 3.7 ትብብር እና ትስስር

### አጠቃላይ ምልከታ

- የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ዘርፍ በሀገር ሁለንተናዊ ዕድገት ላይ ካለው ሚና አንፃር ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከዘርፉ ከሚገኙ ትሩፋቶች ተጠቃሚ እንድትሆን የዓለምአቀፍ ግንኙነትና ትብብር ሥራዎችን ማጠናከር አስፈላጊ ነው፡፡ ለፖሊሲው ትግበራና ለዘርፉ ዕድገት የመንግስትና የግል ተቋማት የእርስ በእርስ ትስስር ሥርዓት ተበጅቶለት የጋራ የልማት ፕሮግራሞች፣ የአቅም ግንባታ፣ የእውቀት እና የቴክኖሎጂ ሽግግር ሥራዎች ሊተገበሩ ይገባል፡፡ የዓለምአቀፍ ግንኙትና ትብብሮችን ለማድረግ በዘርፉ ያሉብን ክፍተቶች በግልጽ የታውቁ አይደሉም፡፡ የሀገራችን ተቋማት ትስስር ሳቢ ምክንያትና አስገዳጅነት የሌለው በመሆኑ፤ ዘርፉ ከሚፈልገው ቅንጅታዊ አሰራር ደረጃ ላይ ያልደረሰና በየተቋማቱ የተግባራት ድግግሞሽ እና የሀብት ብክነትን ያስከተለ ነው፡፡ በመሆኑም የሀገር ውስጥ ተቋማት በጋራ ጉዳዮች ላይ በመተሳሰርና በመቀናጀት የልማትና የአቅም ግንባታ ሥራዎች በጋራ እንዲተገብሩ የሚያስችል የትስስር ማዕቀፍ እንዲኖር ይደረጋል፡፡ እንዲሁም መንግስት የዓለምአቀፍ ግንኙነትና ትብብር ሥራዎችን ለማጠናከር የግንኙነትና ትብብር አድማሱ እንዲሰፋ ያደርጋል፡፡

### ግብ 1፡- የዓለምአቀፍ እና አህጉራዊ ትብብሮችና ትስስሮች ተጠቃሚነትን ማሳደግ

**የአፈፃፀም ስልት**

- ስትራቴጂካዊ ፍላጎቶቻችንን መሰረት ያደረጉ አዳዲስ ትብብሮችና ትስስሮች እንዲመሠረቱ እና ነባሮቹ እንዲጠናከሩ የሁለትዮሽና የብዙህዮሽ ስምምነቶች ይፈጠራሉ፤
- የቴክኖሎጂ ሽግግርና ልማትን የሚያሳልጡ የቴክኖሎጂ አታሼዎች በኢንባሲዎች/ቆንስላዎች እንዲኖሩ የሚያስችሉ ሥርዓት ይዘረጋል፤
- በውጭ ሀገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውንና ትውልደ ኢትዮጵያውን በሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ዘርፍ ልማት ላይ ተሳትፏቸው እያደገ እንዲሄድ ይደረጋል፤
- ከጎረቤት ሀገራት ጋር በዘርፉ ቀጠናዊ ትብብርን የሚያበረታቱ አደረጃጀቶችና የአሠራር ሥርዓቶች ይዘረጋሉ፤
- የነጻና ተደራሽ ሳይንስ (Open science) አሰራሮችና ባህሎች እንዲዳብሩ ይደረጋል፤

### ግብ 2፡- በሀገር ውስጥ ተቋማት መካከል ውጤታማ ትብብርና ትስስር መፍጠር

**የአፈፃፀም ስልት**

- የተቋማትን አጋርነትና ቅንጅት በማሳለጥ ምርትና አገልግሎታቸው በተገቢ ጥራት ተደራሽ እንዲሆኑ ይደረጋል፤
- ሀገራዊ የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ተቋማትን ተወዳዳሪ ለማድረግ ትብብርና ትስስራቸው እንዲጠናከር ይደረጋል፤
- የተቋማት ትስስር በሂደት በገበያውና በጋራ ተጠቃሚነት ላይ ተመስርቶ እንዲመራ ይደረጋል፤
- በተቋማት መካከል የሚፈጠሩ ትብብሮችን ለማሳደግ እንዲሁም የሀብት ብክነትን ለመቀነስ የሚስችሉ የህግ ማዕቀፎች ይዘረጋሉ፤
- በተቋማት የምርምርና የምርት ፍተሻ መሠረተ-ልማት እንዲሁም የሰው ኃይሉን በጋራ መጠቀም እንዲቻል ይደረጋል፤

## 3.8 አካባቢዊ፣ ማህበራዊና ባህላዊ ልማት

**አጠቃላይ ምልከታ**

በሀገራችን የሚለሙም ሆነ ከውጭ ገብተው ጥቅም ላይ የሚውሉ እንዲሁም አገልግሎታቸውን ሲጨርሱ በአግባቡ የሚወገዱበት የአሰራር ሥርዓት በተወሰኑ ቴክኖሎጂዎች ላይ ካልሆነ

በስተቀር በአብዛኛው ሲተገበር አይስተዋልም፡፡ ስለሆነም ቴክኖሎጂዎች ምርትና ማርታማነትን የሚያሳድጉ ከመሆኑ በተጨማሪ በአካባቢና በሕብረተሰቡ ላይ የጎላ ተጽዕኖ የማያሳድሩ፣ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ የአሰራር ሥርዓት መዘርጋት ያስፈልጋል፡፡

የሳይንስ፤ ቴክኖሎጂና ቢዝነስ መሰረት ያደረገ የኢኖቬሽን ልማት እንቅስቃሴ ማህበራዊና ባህላዊ እሴቶቻች ላይ አወንታዊ ተጽእኖ እየፈጠረ የሚሄዱበት የአሠራር ዘዴዎችና አካታች ልማት ለማህበረስብ ደህንነትና ዕድገት አቅጣጫ ሆኖ የቴክኖሎጂን የጎንዮሽ ጉዳቶችን በሚቀንሱ መልኩ እንዲተገበሩ ይደረጋል፡፡ በተጨማሪም የቴክኖሎጂ ልማትና አጠቃቀም ዕድገት ዑደቶች በማህበረሰብ ውስጥ ባህል እንዲሆኑ የአህዝቦት ሥራዎች እንዲጠናከሩና የደህንነት ቁጥጥር እየሠፋ እንዲሄድ ይደረጋል፡፡ እንዲሁም የተለዩ የሀገሪቱ የልማት ዘርፎች ትግበራ አካባቢያዊ፤ ማህበራዊና ባህላዊ ጠቀሜታን የሚያስጠብቁ መሆናቸውን ያረጋግጣል፡፡

## ግብ 1፡- ሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ለአካታች ማህበራዊ ልማትና ባህላዊ ጠቀሜታ ያለውን ሚና ማሳደግ

**የአፈፃፀም ስልት፡-**

- የቴክኖሎጂ አጠቃቀም፣ ደህንነትና ቁጥጥር በማህበረሰብ ውስጥ ባህል እንዲሆን የአህዝቦት ሥራዎች በስፋት ይሰራሉ፤
- የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ልማት አካታች የማህበረሰብ ደህንነትና ዕድገት የአሰራር ሥርዓት ይዘረጋል፤
- ሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ለአካታች ማህበራዊ ልማት የሚኖረውን ሚና ለማሳደግ የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፤

## ግብ 2፡- አካባቢንና ማህበራዊ ደህንነትን መሰረት ያደረገ የቴክኖሎጂ ልማትና ቁጥጥር ማጠናከር

**የአፈፃፀም ስልት፡-**

- የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ልማት እንቅስቃሴ ከማህበራዊና ባህላዊ እሴቶቻችን ጋር ተጣጥመው የሚሄዱበት የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፤
- የጨረራና የኒውክለር ቴክኖሎጂ አጠቃቀምና አወጋገድ ሥርዓት ይዘረጋል፤
- በኬሚካልና በሥነ-ህይወት ቴክኖሎጂ አጠቃቀምና አወጋገድ ሥርዓት ይዘረጋል፤

- በአካባቢና በሰው ልጅ ጤና ላይ የጎንዮሽ ጉዳት የሚያደርሱ ቴክኖሎጂዎች የአገባብ፣ የአጠቃቀምና የአወጋገድ ሥርዓት ይዘርጋል፤

## 4 የፖሊሲው አተገባበርና መርሆዎች

ፖሊሲው በሚከተሉት መርሆዎች ላይ የተመሠረተ ነው፡፡

1. የግሉ ዘርፍ በሳይንስ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ልማትና ትግበራ ውስጥ መሪ እንዲሆን ይደረጋል፡፡
2. ለፖሊሲው ትግበራ የሚውለው ሀብት አመዳደብና አጠቃቀም ውጤታማ፣ ተጠያቂነትና ግልጽነት ያለው እንዲሆን ይደረጋል፡፡
3. በዘርፉ ባለድርሻና ተባባሪ አካላት መካካል ጠንካራ ቅንጅትና ትብብር እንዲኖር ይደረጋል፡፡
4. የፖሊሲው ትግበራ ሃገራዊና አለምዓቀፋዊ ተለዋዋጭ ሁኔታዎችንና መልካም አጋጣሚዎችን ታሳቢ ያደርጋል፡፡
5. በፖሊሲው የትግበራ ሂደት አካታችነት ይረጋገጣል፡፡
6. በተለያዩ አካላት የሚወጡ የሴክተር ፖሊሲዎች ከዚህ ፖለሲ ጋር የተናበቡ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡
7. የቴክኖሎጂ ባለቤትነት እንዲረጋገጥ ይሠራል፡፡

## 5 የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን አስተዳዳር ሥርዓት

ሀገራዊው የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን አስተዳደር ሥርዓት የፖሊሰውን ትግበራ ለመምራት፣ ለመደግፍና ለመከታተል በሚያስችል ሁኔታ ይዘረጋል፡፡ የሳይንስ፣ የቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ሥርዓት ከፌዴራል ጀምሮ እስከታችኛው የአስተዳደር እርከን ድረስ የሚዘረጋ ሆኖ ዋና ዋና ተዋናዮችም መንግስት፣ የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ምክር ቤት፣ የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ዘርፍ፣ ከሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ዘርፍ ቀጥታ የሥራ ግንኙት ያላቸው ባለድርሻና ተባባሪ አካላት፣ የግሉ ዘርፍ፣ የኢኖቬሽን ድጋፍና የምርምር ሥርዓት መካከል የሚኖረው የቴክኒክ፣ የፋይናንስ፣ የህግ፣ የአደረጃጀት፣ መሠረተ-ልማት እንዲሁም የአሠራር መስተጋብሮችን የሚያጠቃልል ይሆናል፡፡

የሀገራዊ የሳይንስ፣ የቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ሥርዓት ተዋናዮች የሚኖራቸው ሚና እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

## 5.1 የመንግስት ሚና

የሳይንስ፣ የቴክኖሎጂና የኢኖቬሽን ሥርዓትን ለኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ዕድገቶች ዋና መሣሪያ ሆኖ አካታች ዕድገት በሚያረጋግጥ መልኩ የተለያዩ የአደረጃጀትና የአሠራር ሥርዓቶችን በመዘርጋት እንዲመራ ያደርጋል፡፡ ለዘርፉ ዕድገት የሚያስፈልጉ የኃብት ምደባ በማድረግ የግሉን ዘርፍ ተሳትፎ እያደገ እንዲሄድ ከአህጉርአቀፍ እና ዓለምአቀፍ ተቋማት ጋር ግንኙነትና ትብብር ያደርጋል፡፡
የዘርፉን ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ውጤታማነታቸውን በመገምገም በአጠቃላይ ለሀገር ውስጥ ምርት የሚኖረው ድርሻ እያደገ በሚሄድ መልኩ የመምራት፣ የማስተባበር፣ የክትልና ግምገማ ሥርዓት ይዘረጋል እንዲሁም የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፡፡

## 5.2 የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ምክር ቤት ሚና

የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ምክር ቤት በህግ የሚቋቋም ሆኖ በዋናነት የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ተግባራት ዘርፍ ተሻጋሪ በመሆናቸው የባለድርሻ አካላትን በማሳተፍ በተናበበና በተቀናጀ መልኩ አቅጣጫ ለመስጠት እንዲያስችለው የቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ልማት ፖሊሲ አፈፃፀምና ውጤታማነት ይከታተላል፣ ይገመግማል፣ ዓላማውን ለማስፈፀም ሴክሬታሪያት፣ የቴክኒክ ኮሚቴ እና እንደአስፈላጊነቱ ሌሎች ኮሚቴዎችን ያቋቁማል፡፡ የምክር ቤቱ ዝርዝር ተግባርና ኃላፊነት በህግ ይወሰናል፡፡

## 5.3 የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ዘርፍ እና ሌሎች የኢኖቬሽን ሥርዓቱ ተዋናዮች

ሀገራዊ የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ፖሊሲ አፈፃፀምና የምክር ቤቱ አቅጣጫዎችን በዋናነት የሚተገበሩት በሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ዘርፍ እና በሚመለከታቸው የመንግሥት ተቋማት ነው፡፡ አላስፈላጊ የሆነ የተግባርና የኃላፊነት ድግግሞሽንና የሀብት ብክነትን ለማስወገድ አስፈላጊው ትብብርና ጥረት ያደረጋል፡፡

በሌላ በኩል ከሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ዘርፍ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ሁሉም ተቋማት በሀገራዊ የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ሥርዓቱ ውስጥ ጉልህ ሚና በሚጫወቱበት መልኩ በሰው ኃይል ልማት፣ በምርምር፣ በቴክኖሎጂ አቅም ግንባታ፣ በምርትና ምርታማነት፣ በዲጂታል ኢኮኖሚ ግንባታ እና በትብብርና ቅንጅት አተገባበር ጉልህ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ይደረጋል፡፡

## 5.4 የግሉ ዘርፍ ሚና

በሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ሥራዎች የግሉ ዘርፍ ሚና ከፍተኛ መሆን ይኖርበታል፡፡ በመሆኑም የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ልማትና ተሳትፎ እያደገ እንዲሄድ የግሉ ዘርፍ በቴክኖሎጂ ልማትና ሽግግር፣ በኢኖቬሽን ልማት እንዲሁም በምርምር ሥራዎች የመሪነት ድርሻ እንዲኖረው ይጠበቃል፡፡ እንዲሁም ዘርፉ በመሠረተ-ልማት ሥራዎች፣ በኃብት ምደባ፣ በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ ከፍተኛ ድርሻ ይኖረዋል፡፡

በመሆኑም በሂደት በመንግስት ይተገበሩ የነበሩ የቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን የልማት ሥራዎች ላይ የግሉ ዘርፍ ተሳትፎ እያደገ እንዲሄድ ይደረጋል፡፡

## 5.5 አጠቃላይ የማህበረሰቡ ሚና

ቀልጣፋና ውጤታማ ምርትና አገልግሎትን ለማግኘት የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ውጤቶችን የሚቀበልና በፍጥነት ከቴክኖሎጂ ጋር በመላመድ ለመጠቀም የሚያስችል ባህል እየዳበረ እንዲሄድ ማህበረሰቡ የበኩሉን ሚና ይጫወታል፡፡

በሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ልማት ሥራዎች ተጠቃሚነትና ተሳትፎ እንዲጎለብት በዕቅድ ዝግጅት፣ በአፈፃፀም ክትትልና ግምገማ ሂደት የህብረተሰቡ ንቁ ተሳትፎ ይኖራል፡፡

# 6 የክትትል፣ ግምገማና የድጋፍ ሥርዓት

## 6.1 ክትትልና ግምገማ

የፖሊሲው እና ስትራቴጂዎች አተገባበር በዘርፉ ልማትና ዕድገት ላይ እንዲመጣ የታሰበውን ውጤት ማምጣት እንዲችል በፖሊሲው አፈፃፀም የሚታዩ ጠንካራና ደካማ ጎኖችን በመለየት የተሻለ ውጤት ለማስመዝገብ እንዲቻል በየደረጃው የክትትል፣ ግምገማና የመማር ሥርዓት ይዘረጋል፡፡ የክትትልና ግምገማ ሥራው ፖሊሲውን መነሻ በማድረግ የተዘጋጁ ማስፈፀሚያ ስትራቴጂዎች፣ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች ላይ የሚያተኩር ይሆናል፡፡

ይህም የፖሊሲ ዓላማዎች፣ ግቦችና ስትራቴጂዎች መሳካታቸውንና ወቅታዊ እርምጃዎች መወሰዳቸውን እንደዚሁም እንደአስፈላጊነቱ የፖሊሲ ክለሳ መደረጉን ለማረጋገጥ ያስችላል፡፡

በብሔራዊ ደረጃ አፈፃፀሙን የማስተባበርና የመከታተል ኃላፊነት የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ሲሆን፤ የመገምገም፣ ውሳኔ እና አቅጣጫዎችን የማስቀመጥ ኃላፊነት የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ምክር ቤት ይሆናል፡፡

በተጨማሪም ከዘርፉ ልማትና ዕድገት ጋር ጥብቅ ቁርኝት ያላቸው የመንግስትና የግሉ ዘርፍ ተቋማት እንዲሁም ክልሎች ለፖሊሲውና ስትራቴጂዎች አፈፃፀም ስኬታማነት የየራሳቸው ድርሻ ያላቸው በመሆኑ በአፈፃፀም ክትትልና ግምገማ ሂደቱ ውስጥ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ይደረጋል፡፡ ዝርዝር አፈፃፀሙ በሚዘረጋው የክትትልና ግምገማ ሥርዓት ይወሰናል፡፡

## 6.2 ለፖሊሲው አፈፃፀም የድጋፍ ሥርዓት

ለሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ፖሊሲ አፈፃፀም ውጤታማነትን ለማረጋገጥ ፖሊሲውን በዋና ባለቤትነት የሚመራው አካል ከመንግስት፣ ከግል፣ እንዲሁም ከዓለምአቀፍ ተቋማት የሚደረጉ የፕሮጀክቶች እና የፈንድ ድጋፍ ሥርዓቶች እንዲኖሩ ያደረጋል፡፡